# Global Storybooks

globalstorybooks.net

## የቩዚ እህት እንደተናገረችው


✎ Nina Orange
Wiehan de Jager
Dawit Girma



This work is licensed under a Creative Commons Attribution 3.0 International License.

https://creativecommons.org/licenses/by/3.0


# የቩዚ እህት እንደተናገረችው


✎ Nina Orange
Wiehan de Jager
Dawit Girma


4

አማርኛ am

አንድ ቀን ጠዋት ቩዚን አያቱ ጠሩትና፣ ‹‹ቩዚ፣ እንካ ይህንን እንቁላል ለወላጆችህ ውሰድላቸው። ለእህትህ ሰርግ ትልቅ ኬክ መስራት ይፈልጋሉና›› አሉት።

የቩዚ እህትም ትንሽ አሰብ አደረገችና እንዲህ አለች፦
‹‹ወንድሜ ቩዚ፣ ስለስጦታ ምንም ግድ የለኝ። ስለኬክም ቢሆን እንዲሁ! ሁላችንም እዚህ በአንድ ላይ አለን። በዚህም ደስተኛ ነኝ። አሁን የክት ልብስህን ልበስ እና ይህን ቀን እናክብር!›› እናም ቩዚ ያደረገው ይህን ነበር።



ወደ ወላጆቹ ዘንድ እየሄደ እያለ ቩዚ ሁለት ልጆች ፍራፍሬ ሲለቅሙ አገኘ። አንደኛው ልጅ የቩዚን እንቁላል ወሰደና ወደዛፉ ወርውሮ አጋጨው። እንቁላሉም ተሰበረ።

‹‹ምንድነው ያደረከው?›› አለ ብዙዓየሁ እያለቀሰ። ‹‹እንቁላሉ እኮ ለኬክ መስሪያ ነበር። ኬኩ ደግሞ ለእህቴ ሰርግ ነበር። አሁን እህቴ የሰርግ ኬክ አለመኖሩን ስታውቅ ምን ትላለች?››



‹‹ምን ይሻለኛል?›› አለ ቩዚ እያለቀሰ። ‹‹ሮጣ የሄደችው ላም ስጦታ ነበረች፣ አናጺዎቹ በሰጡኝ ቄጤማ ፋንታ። አናጺዎቹም ቄጤማውን የሰጡኝ ፍራፍሬ ለቃሚዎቹ የሰጡኝን በትር ስለሰበሩብኝ ለዛ ማካካሻ ነበር። ፍራፍሬ ለቃሚዎቹ በበኩላቸው ያንን በትር የሰጡኝ ለሰበሩብኝ የኬክ ማዘጋጃ እንቁላል ምትክ ነበር። ኬኩ ደግሞ ለሰርጉ ነበር። አሁን እንቁላል የለም፣ ኬክም የለም፣ ስጦታም የለም።››

ነገር ግን ላሟ ወደገበሬው ዘንድ ተመልሳ እየሮጠች ሄደች። ቩዚም ባዶውን ቀረ። ከእህቱም ሰርግ በጣም ዘግይቶ ደረሰ። እንግዶቹም መመገብ ጀምረው ነበር።



ልጆቹ ቩዚን በማናደዳቸው አዘኑ። ‹‹እንግዲህ ኬኩን በመስራት ማገዝ አንችልም፤ ቢሆንም ግን ለእህትህ የሚሆን ምርኩዝ ይሄው›› አለ አንደኛው። ቩዚ ጉዞውን ቀጠለ።

እየተጓዘ እያለም ሁለት ሰዎች ቤት ሲሰሩ አገኘ። ‹‹ይሄን ጠንካራ ምርኩዝ መጠቀም እንችላለን?›› ጠየቀ አንደኛው። ነገር ግን እንጨቱ ለግንባታ የሚሆን ጠንካራ ስላልነበር ተሰበረ።



ላሟም ተስገብግባ ስለበላችበት አዘነች። ገበሬውም ላሟ ለቩዚ እህት ሰርግ ስጦታ ሆና እንድትሄድ ተስማማ። ስለሆነም ቩዚ ተሸከማት።

‹‹ምን ማድረግሽ ነው?›› ሹዚ አለቀሰ። ‹‹ቄጤማው እኮ ለእህቴ ስጦታ ነበር። አናጺዎቹ ምርኩዜን ስለሰበሩ በምትኩ የሰጡኝ ነበር እኮ። ምርኩዙንም ፍራፍሬ ለቃሚዎች እንቁላሌን በመስበራቸው ምክንያት በምትኩ የሰጡኝ ነበር። እንቁላሉም ለእህቴ ሰርግ ነበር። አሁን እንቁላል የለም፣ ኬክም የለም፣ ስጦታም የለም። እንግዲህ እህቴ ምን ትል ይሆን?››



‹‹ምን ማድረጋችሁ ነው?›› ሹዚ አለቀሰ። ‹‹በትሩ እኮ ለእህቴ ስጦታ ነበር። ፍራፍሬ ለቃሚዎቹ የኬክ መስሪያውን እንቁላል ስለሰበሩብኝ በምትኩ የሰጡኝ ነበር። ኬኩም ለእህቴ ሰርግ ነበር። አሁን ግን ምንም እንቁላል፣ ኬክም ሆነ ስጦታ የለም። እህቴ ምን ትል ይሆን?››

አናጺዎቹም በትሩን ስለሰበሩበት አዘኑ። ‹‹እንግዲህ ኬክ በመስራት አላገዝናችሁም፤ ባይሆን ይህ የቤት ክዳን ለእህትህ ይሁን›› አለ አንደኛው። ቩዚም መንገዱን ቀጠለ።



በመንገዱም ላይ፣ ቩዚ አንድ ገበሬና ላም አገኘ። ‹‹እንዴት ጣፋጭ ቄጤማ ነው፣ እንደው ጥቂት መብላት እችል ይሆን?›› ላሟ ጠየቀች። ቄጤማውም ጣፋጭ ስለነበረ ላሟ ሁሉንም በላችው።